ሚያዝያ 28 ቀን 2007 ዓ ም

# አርአያው ምሑር ዶክተር መስፍን አርአያ አርፏል (ከግንቦት 1944 -- የካቲት 2015)




ሀገር ወዳዱና ለአያሌዎች አርአያ የነበረው ዶክተር መስፍን አርአያ በማለፉ ኢሕአፓ የተሰማውን መሪር ሐዘን በዚህ መልዕክት አማካይነት እየገለጸ ቤተሰቡና ወዳጆቹ ሁሉ እንዲጽናኑ መልዕክቱን ያስተላልፋል። ዶክተር መስፍን አርአያ በአካለጉዛይ ኤርትራ ተወልዶ በልጅነቱ ዕድሜ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጨርሷል። በዚያን ወቅት ቀኃስ ዩኒቨርስቲ በአሁኑ ወቅት ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብቶ በፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። ዶ/ር መስፍን በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መሉ ተሳትፎ የነበረውና በምስጢራዊ እንቅስቃሴዎች በአስተማማኝነት የተሳተፈ ጽኑ ኢትዮጵያዊ ነበር። በ1965 ዓ. ም (1972) ወደ አሜሪካ ተጉዞ በዚያም በኢትዮጵያ የትግል እንቅስቃሴ አኩሪ ተሳትፎን አድርጓል። መስፍን ከኩኒ ድህረ ምረቃ ማአከል (Cunny Graduate Center)--ኒው ዮርክ- እአአ በ1988 በፖለቲካል ሳይንስ የዶክርተነት ዲግሪውን አግኝቷል። እአአ ከ1994 ዓ.ም. ጡረታ እስከወጣበት 2013 ዓ.ም. ድረስ በተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ በዮርክ ኮሌጅ

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

የሶሻል ሳይንስ ዲፓርትመንት ውስጥ (York College Department of Social Science) በአፍሪካ ጥናት ክፍል በኃላፊነት አስተምሯል። መስፍን በኢትዮጵያ በተለይም በምስራቅ አፍሪካ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ጥናቶችን ያደረገና በዚህም ላይ በርካታ ጹሁፎችን ያበረከተ ምሁር ነበር። ጹፎቹም በተለያዩ የኢትዮጵያውያን መጽሄቶችና ድረገጾች፤ በጆርናል ኦፍ ኖርዝ ኢስት አፍሪካን ስተዲስ (Jornal of North East African Studies) እንዲሁም ጆርናል ኦፍ ሞደርን አፍርካን ስተዲስ (Jornrnal of Modern African Studies) በሚባሉ መጽሔቶች ላይ ስፍረዋል። መስፍን በትግል ባሳለፈበት ጊዜ ሁሉ በጽናትና በቆራጥነት የሻዕቢያን የቅኝ ግዛት ጥያቄ አቋም ያጋለጠና የኤርትራን የመገንጠል ጥያቄ የተቃወመ፤ ኢትዮጵያዊነቱን ጠብቆና አጠንክሮ የታገለ ጀግና ነበር። የወሰደው ቆራጥና ጽኑ አቋሙ በእሱና በቤተሰቡ ላይ ብዙ ችግርና መከራ ያደረሰበት ቢሆንም እስከመጨረሻው ግንባሩን ሳያጥፍ የቆመና የታገለ ጀግና መሆኑን ወዳጆቹ ይመሰክሩለታል። ውይይትና ጨዋታ ወዳድ የሆነውና ከብዙዎች በቀላሉ ይግባባ የነበረው መስፍን በውጭ አገር የወያኔና የሻዕቢያን አገዛዞች በመቃወምና በመታገል በኩል ተጨባጭ አስተዋጾ አድርጓል። መስፍን በነበረውም ሆነ ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያዊነቱን አስከብሮ (የባዕድ ዜጋ መሆንን እምቢኝ ብሎ) ህይወቱ ያለፈች ብትሆንም በተደረገበት ልዩ ልዩ ተጽዕኖ ሀገሩን ሳይክድ የቆየ ከመሆኑ ሌላ በትግሉ መስከ ኢሕአፓን በተጨባጭ ደግፎ የታገለ መሆኑ መጠቀስ ያለበት ነው።



በተለያዩ ቦታዎች በኢሕአፓና በኢሕአፓ አባላት በተዘጋጁ ስብሰባዎች ላይ ተጋብዞ ስለ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታም ሆነ ስለወያኔ ሻዕቢያ ባህሪዎችና ተግባራት ፖለቲካዊ ትንታኔዎች በመስጠት ለታዳሚው ግንዛቤዎችን ሰጥቷል።

ዶክተር መስፍን የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት ልጅ አባት ነው። ትሁትና ሕዝብ አፍቃሪ የሆነው መስፍን ሲለየን በአያሌው የሚያጓድል የሚጎዳን መሆኑን በሀዘን እንገነዘባለን። ዶክተር መስፍን አርአያ በህይወቱ ባበረከተው አስተዋጽኦ እና ይዞት በቆየው ጽኑ ኢትዮጵያዊ አቅዋሙ የሚዘከር ነውና ሞተ ሳይሆን ተለየን ብለን የምናስታውሰውና ሌሎችም የእሱን አርአያነት ተቀብለው ትግሉን እንዲቀጥሉ የምንጠራበት ነው።

ለዶክተር መስፍን አርአያ ቤተሰብ ጽናቱን ይስጣችሁ እንላለን!
ጀግናው ኢትዮጵያዊ ምሁር ዶክተር መስፍንን አንረሳውም !!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France